# <u>ለማሳለፍ ዕጣ</u>

(አንሙት ከለንደን)

አሁን ላይ ተረግጠን፣
ነገን እየጠበቅን፣
ለማሳለፍ ዕጣ፣ በወረፋ ቆመን፣
ጊዜን ፍራሽ  አርገን ፣
ለጊዜም አንብተን፣
ኖሮ ቀባሪዎች ፣
ዕዝን ተቀምጠን ፣
ባናት ባናቱ ላይ
ጀግኖች እየቀበርን፣
እነሱ በህይወት፣ እኛ በእንባ ከፍለን
ትላንት በስቲያ፣ ትላንት፣ ዛሬንም እየኖርን፣
ካለንበት ዘመን፣
ካለነው ተኻተን፣
ማን ይሆን?!
ምን ይሆን የሚቀሰቅሰን?!

ከእንግዲህ ይበቃል! ቴዎድሮስን አናንሳ!
የሰጠ እጁን ለእጁ፣ ለክብሩ እሚሳሳ!
ከእንግዲህ አንጥራው!  ዮሐንስም ይብቃው!
ለመተማ ግብር፣ አንገቱን የሰጠው!
ከእንግዲህ ይበቃል! በላይን አንጥራው!
ለአርበኝነት ዋጋው፣ ገመድ የከፈልነው!
ከእንግዲህ ይበቃል! ኃይምን አንጥራ!
አሥራትን፣ አሰፋን፣ ተሥፋዬን፣ ሽብሬን፣ ሌሎችን አንጥራ፣
ሆነዋል አፈሩን፣ የአፈር ውስጥ አንጡራ፣
ባካልም ቢሞቱ! አልሞቱም እነሱ፣
ቋሚ ሀውልት ነው፣ ታሪካቸው ቅርሱ፣
ጠባቂ አልባ ሲሆን፣ ክፍት ሲያድር በሩ፣
ሀውልቱን ለማጥፋት፣ በመንቀል ከሥሩ፣
ቋራ አፈር ላይ ሱዳን፣ ሲረግጥበት እግሩ
ይልቅስ አሁን ነው፣ ያሉ እያጣጣሩ።
ጎበዝ እንቅልፍ ይብቃ፣ ጎበዝ ተጠራራ!
ጠመንጃህን አንሳ፣ ምረጥ ያገር  አውራ!